# እ.ኤ.አ. ኤፕሪል 1-10/2010 የነበረው


# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበረው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፉት አስር ቀናት በምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ፣ በሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በአፋር ክልል ዞን 3፣ 4 እና 5፣ በሲቲ፣ በፋፈን፣ በደገሃቡር፣ በሊበን፣ በአፍዴር እና በቆራሄ፣ በኢሉአባቦራ፣ በጅማ፣ በምስረቅ ወለጋ፤ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በአርሲ እና ባሌ እንዲሁም በጉጂ እና ቦረና፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በሲዳማ፣ በወላይታ፣ በጋሞጎፋ፣ በሰገን ህዝቦች፣ በደቡብ ኦሞ፣ በጌዴኦ፣ በቤንች ማጂ እና በከፋ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበባቸዉ ሲሆን በቡርቃ እና በጅግጅጋ ጣቢያዎች ላይ ከባድ እና ጎርፍ የማስከት አቅም የነበረዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ውሰጥ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በቡርቃ 102.9፣ በጅግጅጋ 79.4፣ በአሮሬሳ 62.7፣ በጂንካ 74.8 እና 52.5፣ በአብኣላ 64.8፣ በከምባ 55.5፣ በተርጫ 54.2፣ በነገሌ ቦረና 52.4፣ በገዋኔ 50.0፣ በሳዉላ 49.4፣ ቀብሪደሀር 30.2 እና በደገሃቡር 37.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-201 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከአፋር ዞን 1፣ 3 እና 5፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሸዋ፣ አርሲና ባሌ እንዲሁም የምስራቅ ሀረርጌ፤ ከትግራይ የደቡብና የሰሜን ትግራይ፤ ከአማራ ደቡብና ሰሜን ወሎ፣ዋግህምራ፣ ኦሮሚያ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ሶማሌ ክልል የጅግጅጋ፣ የደገሀቡር፣ ቆራሄ፣ ዋርዴርና የአፍዲር ዞኖች በተጨማሪም ድሬዳዋና ሀረሪ እንዲሁም አዲስ አበባ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከትግራይ የመካካለኛውና የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ እና የአዊ ዞን የኦሮሚያ ክልል የምዕራብና ምስራቅ ወለጋ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፤ ከአፋር ክልል የዞን1 ምስራቃዊው ክፍል እንዲሁም ከሶማሌ ክልል የፊቅ ዞን ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል ( ካርታ 1 እና 2 )፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የምዕራባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ዳርቻ፣ ከአማራ የደቡብ ጎንደር እንዲሁም ከኦሮሚያ የቦረና ዞን ምዕራባዊው ክፍል በስተቀር የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት አሥር ቀናት ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበረው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፉት አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተገኘው እርጥበት የተሻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የበልግ እርሻ ስራ እንቅስቃሴ እያካሄዱ ላሉ አካባቢዎች ለሰብሉ የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትና የዘር ጊዜ እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። ሆኖም ግን በአንዳንድ አካባቢዎች የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በተለይም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች (በቡርቃ እና በጅግጅጋ ጣቢያዎች) ላይ ከባድ እና ጎርፍ የማስከትል አቅም የነበረዉ ዝናብ ተመዝግቧል። ይህም ሁኔታ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚኖረውን የዉሃ አቅርቦት ያሻሽለዋል (ካርታ 4)።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ
## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የተሻለ የእርጥበት ገፅታ የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛው ኦጋዴን፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ መካከለኛውና የላይኛው ሽምጥሸለቆ፣ መካከለኛና የላይኛው ገናሌዳዋ፣ አብዛኛው ኦሞጊቤና የላይኛው አፋር ደናክል ተፋሰሶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ የታችኛው ዋቢሸበሌ፣ አብዛኛው ገናሌዳዋ፣ የምዕራብ አዋሽ፣ መካከለኛውና የታችኛው አባይ፣ የምስራቅና የታችኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛው ኦሞጊቤ እንዲሁም ጥቂት የታችኛው ተከዜ አዋሳኝ ቦታዎች ሲሆኑ፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል(ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2018 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20/2018 የሚኖረው

## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት ከቀዳሚ አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡

በመጪው ኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተለይም በበልግ ዝናብ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፤ አርሲና ቦሌ፣ ቦረናና ጉጂ፤ አዲስ አበባ፤ ጋምቤላ፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ የሶማሌ ክልል፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ፣ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች፤ የአፋር ዞን 1፣3 እና 5 መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከሚኖሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በተጨማሪም የምሥራቅ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ ጎንደር ዞኖች እንዲሁም ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ፡፡

## እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በተገለፀው ትንበያ መሰረት በተስፋፋ መልኩ ሊገኝ የሚችለው እርጥበት ተዘርተዉ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ልዩ ልዩ የበልግና የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚኖሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ሥፍራዎች የሚጠበቀዉ ከባድ ዝናብ በወቅቱ የሚኖረውን የዉሃ አቅርቦት እንደሚያሻሽል ከመጠበቁም በተጨማሪ የሚመለከተዉ ክፍል የሚገኘዉን

ከፍተኛ እርጥበት ጥቅም ላይ ለማዋል የተለያ የዉሃ ማቆር ዘዴዎችን አጠናክሮ  ቢሰራና እጥረት በሚገጥምበት ጊዜ በአንዳንድ ማሣዎች ላይ ዉሃዉን ለመጠቀም ይረዳል።

በሌላም መልኩ የሚጠበቀዉ ከባድ ዝናብ በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረዉ ስለሚችል የሚመለከተዉ አካል አስፈላጊዉን ጥንቃቄ እንዲያደርግ ይመከራል ።

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለዉ የኤፕሪል ሁለተኛው አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ካለፈው አስር ቀናት የተሻለ የዝናብ ስርጭትና መጠን ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማል። በዚህ መሰረት አብዛኛው የታችኛውና የመካከለኛው ተከዜ፣ ጥቂት አዋሳኝ የደናክል፣ የታችኛው አባይና አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ባሮአኮቦ፣ ገናሌዳዋና ኦሞጊቤ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች በአብዛኛው መደበኛና ጥቂት ቦታዎች ደግሞ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።  ከዚህም በተጨማሪ የአባይ ሰሜናዊ እና ምስራቃዊ ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ  መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖረውቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል።